ከእነዚህ መካከል የታላቁ ሊቅ የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ገዳምን መልሶ ለማቋቋም የተደረገው ርብርብ እንዲሁም የአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ሙዓለ ሕፃናት ግንባታ እና ሌሎችም የሚጠቀሱ ናቸው፣

ለሰ/ት/ቤቶች የተለያዩ ሥልጠናዎችን ማዘጋጀት እንዲሁም ከብሔራዊ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር የተጀመረው ኘሮጀክት ተጠናክሮ እንዲቀጥል እየተደረገ ያለው ጥረትና ሌሎችም ዋነኞቹና የሚጠቀሱት ናቸው፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን የአገልግሎት ማስፈጸም አቅሙ እያደገ በመምጣቱ ወረዳ ማእከላት ወደ ማእከልነት እንዲያድጉ፣ መምህራን የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠና እንዲወስዱ እንዲሁም በውጪ ያለች ቤተክርስቲያን የአገልግሎት ችግር እንዳይገጥማት በአባላት በኩል አገልግሎት እንድታገኝ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡



*በማኅበሩ የሠለጠኑ ከጋምቤላ ክልል የመጡ ተተኪ መምህራን*

ከሁሉም በላይ ማኅበሩ አሁን እየሰጠው ያለ አገልግሎት በተሻለ መልኩ እንዲቀጥል ለማድረግ የራሱ ሕንፃ ሊኖረው ግድ ስለሆነ የጽ/ቤት ሕንጻ በአፋጣኝ እየተገነባ ይገኛል፡፡ እስከአሁን 7ተኛ ፎቅ ላይ የደረሰው ሕንፃው ተጠናቆ ሙሉ በሙሉ አገልግሎት ለመስጠት 5.8 ሚሊዮን ብር አካባቢ ያስፈልገዋል፡፡

የጽ/ቤት ግንባታው ቶሎ መጠናቀቅ ማኅበሩ ለሚኖረው አገልግሎት ወሳኝ መሆኑ ይታመናል፡፡ ሕንፃውን ለመፈጸም ሁላችንም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ልንረባረብ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ማኅበረ ቅዱሳን በ2002 ዓ.ም ግማሽ መንፈቀ ዓመት በስብከተ ወንጌል፣ በግቢ ጉባኤያት፣የቤተክርስቲያንን አስተዳደር በማጠናከር፣ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ተሳትፎ በማድረግ ሥርዓተ ትምህርት በመቅረጽ ያደረጋቸው የአገልግሎት እንቅስቃሴዎች የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ ወደ ፊትም ከአሁኑ የተሻለ እንዲንቀሳቀስ በማድረግ ሁሉም በየአገልግሎት ዘርፉ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡



*የሐመር ብሔረሰብ ተወላጆች ሲጠመቁ*

**ቤተክርስቲያንን በጋራ እናገልግል**

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# በኢ/ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን


*በማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት የተዘጋጀ*
*ፖ.ሣ.ቁ 80078*
*ስልክ —0116554776*
*E-mail Mkpublicrelation@gmail.com*
*www.eotc-mkidusan.org*
*አዲስ አበባ*

*ግንቦት ፳፻፪ ዓ.ም*

# በ2002 ዓ.ም ማኅበረ ቅዱሳን ምን ሠራ?

***እንኳን ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም በዓለ ልደት እና ለማኅበረ ቅዱሳን የምሥረታ በዓል በሰላም አደረሰን፡፡***

ማኅበረ ቅዱሳን በአገር ውስጥ 41 ማእከላት፣ 404 ወረዳ ማእከላት እና ግንኙነት ጣቢያዎች፣ ከ250 በላይ ግቢ ጉባኤያት በውጪ ሀገራት ደግሞ 4 ማእከላትና 5 ግንኙነት ጣቢያዎችን በማዋቀር አገልግሎት እየሰጠ ነው ፡፡

ማኅበሩ ከተቋቋመበት ዓላማ አንጻር እየሠራ ያለው ሥራ ሊያስመሰግነው የሚገባ ቢሆንም ካለው የአባላቱ ትጋትና ተሳትፎ የሙያ ስብጥር እንዲሁም በምእመናን ዘንድ ካለው ሰፊ ተቀባይነትና እገዛ አኳያ ወደፊት ብዙ ሊያከናውናቸው የሚገቡ ተግባራት እንዳሉ ይታመናል፡፡

በመሆኑም ያለፈውን የአገልግሎት አካሔድ በመገምገም የወደፊቱን አቅጣጫ መተለም አስፈላጊ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በዚህም መነሻነት ማኅበሩ በ2002 ዓ.ም ምን ሠራ? ማኅበረ ቅዱሳን ከተቋቋመባቸው እና ከተመሠረተባቸው ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን ማዳረስና ማስፋፋት ነው፡፡

ስለዚህ በ2002 ዓ.ም በደቡብ ምዕራብ እና ምዕራብ ኢትዮጵያ ከተሞች ሐዋርያዊ ጉዞ በማድረግ ሰፊ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ሰጥቷል፡፡

እንዲሁም በተለያዩ የብሔር ብሔረሰብ ቋንቋዎች የሰባክያነ ወንጌል ስልጠናዎችን ሰጥቷል፡፡ በተለያዩ ቋንቋዎች የስብከት፣ የመዝሙር ካሴቶችና መጻሕፍትን አሳትሟል፡፡ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ እያሉ የሚያጋጥሟቸውና ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ችግሮችን እንዴት መወጣት እንዳለባቸው የሚያግዝ ምክክር ከግቢ ተማሪዎች ጋር አድርጓል፡፡

ከማኅበሩ የአገልግሎት ዘርፎች አንዱ ቤተክርስቲያንን በሙያ ማገልገል ነው፡፡ በመሆኑም ቤተክርስቲያን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ሊኖራት የሚገባውን ተጠቃሚነት



*በማኅበሩ የሠለጡኑ ከባሌ፣ወላይታ፣ዳውሮና ደቡብ ኦሞ ሀገረስብከት የመጡ ሠልጣኞች ዝማሬ ሲያቀርቡ*

ለማጠናከር ሁሉም ባለው ሙያ እንዴት ማገልገል እንዳለበት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ምክክር ተደርጓል፡፡

ቤተክርስቲያን እስከ ዛሬ የነበራትን የአገልግሎት ሒደት በሳይንሳዊ ሒደት ለመደገፍ በጥናትና ምርምር ማእከል በተደጋጋሚ ዐውደ ጥናቶች ተካሒደዋል፡፡ ይህም ነጻ የሙያ አገልግሎት ለቤተክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልእኮ ያለውን አስተዋጽኦ የሚያሳይ ዐውደ ጥናት ነው፡፡

የቤተክርስቲያን አስተዳደር የተጠናከረ እንዲሆን ከማገዝ በተጓዳኝ በቤተክርስቲያን ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ማኅበረ ቅዱሳን ንቁ ተሳትፎ አድርጓል፡፡ በፕሮጀክቶች ቀረጻና ትግበራ፣ የአብነት ት/ቤቶችን መልሶ በማቋቋም፣ ገዳማውያንን እና አረጋውያንን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሥራዎችን ሠርቷል፡፡



*የተጠመቁ የሐመር ብሔረሰብ አባላት*